# በዘር በሩካቤ መውለድ ወይም መወለድ ወንጀል አይደለም። ወንጀለኛም አያደርግም። በረከት ነው።

**“ወተወክፎ ለእስራኤል ቍልዔሁ ወተዘከረ ሣህሎ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ ለአብርሃም ወለዘርዑ እስከ ለዓለም።”** “ባርያውን እስራኤልን ተቀበለው፤ ይቅርታውንም ዐሰበ፤ ለአባቶቻችን ለአብርሃምና ለዘሩ እስከ ዘለዓለም አደርገዋለኹ ያለውን።” (ሉቃ፤ ፩፡ ፶፬ እና ፶፭።) ይኽ ቃል ከቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ የተነገረ ቃል ነው። በዘር በሩካቤ መውለድ፥ መወለድ፥ ሰው ኾኖ መገኘት በደል ቢኾን ኖሮ፤ ለአባቶቻቸን ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘለዓለም አደርገዋለኹ ያለውን ይቅርታውን ዐስቦ ባርያውን እስራኤልን ተቀበለው፤ ባላለች ነበር።

በዘር በሩካቤ መውለድ፥ መወለድ ለሰው በጥንተ ፍጥረት የተሰጠ በረከት ነው። **“ወገብሮ እግዚአብሔር ለዕጓለ እመሕያው በአምሳለ እግዚአብሔር ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ። ወባረኮሙ እግዚአብሔር ወይቤሎሙ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር ወቅንይዋ ወኰንንዎሙ ለዓሣተ ባሕር ወለአራዊተ ምድር ወለአዕዋፈ ሰማይ ወለኵሉ እንስሳ ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር።”** “እግዚአብሔር ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አደረጋቸው። ባረካቸው፤ እንዲኽም አላቸው፤ ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉአት፤ ግዙአት፤ የባሕሩን ዓሣ፥ የምድርን አራዊት፥ የሰማዩን ወፉን አሞራውን፥ እንስሳውን ኹሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውን ኹሉ ግዙ ብሎ ባረካቸው።” (ዘፍ፤ ፩፡ ፳፯ እና ፳፰።)

**“ዝ መጽሐፈ ፍጥረተ ዕጓለ እመሕያው፤ ወበዕለት አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም በአምሳለ እግዚአብሔር ገብሮሙ ተባዕተ ወአንስተ ወባረኮሙ። ወሰመየ ስሞ አዳም በዕለት እንተ ባቲ ፈጠሮሙ።”** “የአዳም (የሰው) ትውልዱ መጽሐፍ ይኽ ነው፤ እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሳሌ አደረገው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ባረካቸውም። ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራው።” (ዘፍ፤ ፭፡ ፩ እና ፪።) ይኽ ነው የሰው ዘር የሕይወቱ መሠረት። ሲባዛ የሚኖረውም በዚኽ መሠረት ነው። በዚኽ ኃጥእና ጻድቅ አይለይበትም። በዚኽ ዕገሌ ጻድቅ፥ ዕገሌ ኃጥእ አይባልም። ከዚኽ በኋላ ግን ሰው በእምነቱ፥ በሥራው ሊመረጥ፥ ላይመረጥም ይችላል። አብርሃም አመነ፤ ጽድቅ ኾኖ ተቈጠረለት። ይኽ ብቻ አይደለም። ዘሩ እንደ ሰማይ ኮከብ፥ እንደ ባሕር አሸዋ እንዲበዛ ተነገረለት። በዚኽ ውስጥም በሥራ፥ በሃይማኖት የተለያዩ አሉ። ከዚኽ ጋር ለአብርሃም፤ በዘርኽ አሕዛብ ኹሉ ይባረካሉ፤ የሚል ልዩ ስጦታ ተሰጠ። ይኽ እንግዲኽ ከሥራና ከእምነት በላይ በእግዚአብሔር ሥራና ሥልጣን የተወሰነ ነው። ለኹሉ አልተሰጠም። ለአንድ ብቻ ነው። ለቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ ማርያም። አምላክን በመውለዷ። ይኽን ይዞ ተስፋው በትውልድ ዘምቷል። “ከይስሐቅ ዘር ይጠራልኻል። ያዕቆብን ወደድኩ። ለእሱ የተነገረው ተስፋ እስኪፈጸምለት ድረስ ምስፍናና ግዛት ከይሁዳ አይጠፋም። ከሆድኽ ፍሬ በዙፋንኽ አነግሥልኻለኹ።” እነዚኽ የተስፋ ቃላት በየጊዜው ለተስፋ መዝመቻ መሥመሮች የተነገሩ ናቸው።

ይኽን ተከትሎ ስለ ከፍተኛው ምርጫ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለያዕቆብ በራእይ ገለጸ። ያዕቆብ ከሶርያ ወደ አገሩ ለመመለስ በጉዞ ላይ ነበር። ያቦቅ ከተባለው ወንዝ ሲደርስ ጊዜው መሽቶ ስለ ነበር ቤተ ሰቡን በሙሉ አሻግሮ እሱ ከማዶ ዐደረ። በዚያች ሌሊትም ታላቅ ራእይ አየ። **“ወተርፈ ያዕቆብ ባሕቲቱ ወተጋደሎ ብእሲ እስከ ጽባሕ። ወሶበ ርእየ ከመ ኢክህሎ አኀዘ ሥርዎ ሕሩመ እንዘ ይትጋደል ምስሌሁ። ወይቤሎ ፈንወኒ እስመ ጎህ**

**ጽባሕ፤ ወይቤሎ ኢይፌንወከ ለእመ ኢባረከኒ። ወይቤሎ መኑ ስምከ ወይቤሎ ያዕቆብ ስምየ። ወይቤሎ ኢይኩን እንከ ስምከ ያዕቆብ፤ ዳእሙ ይኩን ስምከ እስራኤል፤ እስመ ክህልከ ምስለ እግዚአብሔር ወምስለ ዕጓለ እመሕያው። ወይቤሎ ያዕቆብ አይድዐኒ ስመከ፤ ወይቤሎ ለምንት ለከ ትሴአል ስምየ እስመ መድምም ውእቱ፤ ወባረኮ በህየ። ወሰመዮ ያዕቆብ ስሞ ለውእቱ ብሔር፤ ራእየ እግዚአብሔር እስመ ይቤ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ገጸ በገጽ ወድኀነት ነፍስየ ወገጽየ። ወሠረቀ ፀሓይ ሶበ ኀደጎ ራእየ እግዚአብሔር ወሎቱሰ ያስኦዝዞ እግሮ።”** “ያዕቆብ ብቻውን በዚያ ዐደረ፤ አንድ ሰውም እስኪነጋ ይታገለው ነበር። እንዳላሸነፈውም ባየ ጊዜ የጭኑን ሥር ቈንጠጥ አድርጎ ያዘው። ከእሱ ጋር በሚታገልበት ጊዜ፤ ነግቷልና ልቀቀኝ አለው፤ እሱም ካልባረክኸኝ አልለቅኽም አለው። ታጋዩ፤ ስምኽ ማነው፤ አለው፤ ያዕቆብም ስሜ ያዕቆብ ነው አለው። ከእግዲኽ ወዲኽ ስምኽ ያዕቆብ አይባል፤ ስምኽ እስራኤል ይባል፥ ይኹን እንጂ፤ ከሰውም ከእግዚአብሔርም መኾን ተችሎኻልና አለው ታጋዩ። ያዕቆብም በፈንታው ታጋዩን፤ የአንተስ ስምኽ ማነው፤ አለው፤ ስሜን ለምን ትጠይቃለኽ፤ ስሜ ድንቅ ነውና አለው፤ በዚያም ባረከው። ያዕቆብም የዚያን ቦታ ስም እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አይቼዋለኹ ሰውነቴም ከመከራ ዳነች ብሎአልና ራእየ እግዚአብሔር፤ እግዚአብሔር የተገለጠበት ቦታ፤ አለው። የእግዚአብሔር ራእይ በተወው ጊዜም ፀሓይ ወጣ፤ እሱን ግን እግሩን ደንዝዞት ነበር።” (ዘፍ፤ ፴፪፡ ፳፬- ፴፪።)

ይኽ ከዚኽ በላይ የገለጽነው ነገረ ራእይ፤ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የኾነበትን የመለኮትንና የትስብእትን ምስጢረ ተዋሕዶ የሚያሳይ ነው። ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር መኾን ተችሎኻል፤ ነው ያለው። ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ኾኖ፤ የያዕቆብን ደም ግባት ወደደ፤ የተባለ አምላክ ከልጁ ተወልዶ ስለ ተገለጸ ነው። እሷም ይኽን ለማዘከር ወደ ላይ ኼዳ፤ ባርያውን እስራኤልን ተቀበለው፤ አለች። ለተዋሕዶ መረጠው ማለት ነው።

የምርጫ ነገር ቀደም ብለን እንደ ገለጽነው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በሰው ዐሳብ አይመጠንም፤ አይወሰንም። ምናልባት በየ ጊዜው፥ በየ ቀኑ ስለ ተወለዱ ሰዎች ስንናገር፤ በተባረከ ቀን፥ በተባረከ ሰዓት ተፀንሶ፥ ተወልዶ ነው ብለን እንናገር ይኾናል። ግን እንዲኽ ሳይኾን ይገኛል። የይስሐቅ ባለቤት ርብቃ የወለደችው አንድ ጊዜ ነው። ዕለተ ፅንስ፥ ዕለተ ልደት አንድ ጊዜ ነው። በዚያው በአንዱ ዕለተ ፅንስ መንታ ፀነሰች፤ በዚያው በአንዱ ዕለተ ልደት መንታ ወለደች። ልጆች በማሕፀኗ ይጣሉ ነበር፤ ይታገሉ ነበር። ተጨነቀች። በጊዜው ወደ ነበረው ወደ ታላቁ ካህን መልከ ጼዴቅ ኼዳ ችግሯን ነግራ እንዲጸልይላት ጠየቀችው። ታላቁ ካህንም ጸለየላት፤ ባረካት። ስለ ልጆቹም ዕድል እንዲኽ አላት። እዚኽ ላይ ኦሪት ዘፍጥረትና መጽሓፈ ቀሌምንጦስ በሰጡት አነጋገር ውጥንና ሙሉ ዐሳብ የሚታይበት ጽሑፍ ይገኛል።

ሀ፤ በኦሪት ዘፍጥረት ፳፭፡ ፳፪ እና ፳፫፤ **“ወሖረት ትሰአል ኀበ እግዚአብሔር። ወይቤላ እግዚአብሔር ክልኤቱ ሕዝብ ሀለዉ ውስተ ከርሥኪ ወክልኤቱ ሕዝብ ይወፅኡ እምከርሥኪ፤ ወሕዝብ እምሕዝብ ይኄይስ ወዘየዐቢ ይትቀነይ ለዘይንእስ።”** “ከእግዚአብሔርም ትጠይቅ ዘንድ ኼደች። እግዚአብሔርም አላት፤ ኹለት ሕዝብ በማሕፀንሽ አሉ፤ ኹለት ሕዝብ ከማሕፀንሽ ይወጣሉ፤ አንዱ ከአንዱ ይበልጣል፤ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል።”

ለ፤ በመጽሓፈ ቀሌምንጦስ ደግሞ፤ **“ወሶበ ኮኖ ለይስሐቅ ፷ ዓመተ ፀንሰት ብእሲቱ ርብቃ። ወሶበ በጽሐ ጊዜ ወሊዶታ ሖረት ኀበ መልከ ጼዴቅ ባረከ ወጸለየ ላዕሌሃ ወአስተብቍዐ በእንቲአሃ ወይቤላ እግዚአብሔር ልዑል ረሰየ ውስተ ከርሥኪ ፪ ተባዕተ ወእሙንቱ ይከውኑ ፪ ሊቃውንተ ላዕለ ፪ ሕዝብ ዐበይት ወዘየዐቢ ይትቀነይ ለዘይንእስ ወይጻልዑ በበይናቲሆሙ ወአልቦ ማእከሌሆሙ ፍቅር ወእምውሉዱ ዘየዐቢ ይቀትል እኅዋሁ እምትዝምደ ካልኡ ወአነ እትቀነይ ለውእቱ ብእሲ ወይሰመይ ስሙ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ወይሰቀል ዲበ ዕፅ ወያአትት መርገመ።”** “ይስሐቅ ፷ ዓመት

በኾነው ጊዜ ሚስቱ ርብቃ ፀነሰች። የምትወልድበት ሰዓት በደረሰ ጊዜም ወደ መልከ ጼዴቅ ኼደች፤ ባረካት፤ ጸለየላት፤ ስለ እሷ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ፤ ማለደ። ልዑል እግዚአብሔር በማሕፀንሽ ኹለት ወንዶች ልጆች ፈጥሯል። እነሱም ለኹለት ታላላቅ ሕዝብ አባቶች ይኾናሉ። ታላቁ ለታናሹ ይገዛል። እስ በሳቸው ይጣላሉ፤ በመኻከላቸው ፍቅር የለም። ታላቁ ከሌላው ወገን የኾነውን ይገድላል። እኔ ለዚያ ሰው እገዛለኹ፤ ያን ሰው አገለግላለኹ፤ ስሙ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ይባላል፤ በዕንጨት ላይ ይሰቀላል፤ መርገመ ሥጋ፥ መርገመ ነፍስን ያርቃል፤" ብሎ ነግሯታል።

እንደ ተናገረ ኹለት ልጆች ተወለዱ። ዔሳውና ያዕቆብ። ኹለቱም የታላላቅ ሕዝብ አባቶች ኾኑ፤ የዐረብና የእስራኤል። ግን ሳይወለዱ፥ ክፉና መልካምም ሠርተው ይኽ ከመታወቁ በፊት እግዚአብሔር፤ ዔሳውን ጠላኹ፤ ያዕቆብን ወደድኹ፤ አለ ይላል መጽሐፍ። (ሚል፤ ፩፡ ፪።) ይኽንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስፋፍቶ፤ የምርጫ ነገር በእግዚአብሔር ዐሳብ ብቻ የሚወሰን መኾኑን ገልጾ በሮሜ ፱ ትምህርት ሰጥቶበታል። እንዲኽ ይላል። "እስመ አሰፈዎ ወይቤሎ አመ ከመ ዮም እገብእ ኀቤከ፤ ወትረክብ ሳራ ወልደ። ወአኮ ባሕቲታ ዓዲ ርብቃኒ ፀንሰት መንታ ለይስሐቅ አቡነ። ወዘእንበለ ይትወለዱ ወይግበሩ ሠናየ ወእኩየ ከመ ይትዐወቅ በምንት እንከ ኀርዮቱ ለእግዚአብሔር። ከመ ያእምሩ ከመ ኢኮነ በምግባሩ ለሰብእ ዘእንበለ ዳእሙ ዘውእቱ ጸውዐ፤ ወይቤላ ለርብቃ ዘየዐቢ ይትቀነይ ለዘይንእስ። እስመ ከማሁ ጽሑፍ ያዕቆብሀ አፍቀርኩ ወዔሳውሀ ጸላእኩ።" "ከርሞ እንደ ዛሬ ወደ አንተ እመለሳለኹ፤ ሳራም ወንድ ልጅ ታገኛለች፤ ብሎ ተስፋ ሰጥቶታልና። ግን እሷ ብቻ አይደለችም፤ ርብቃም ለአባታችን ለይስሐቅ መንታ ፀነሰች እንጂ። ሳይወለዱ ክፉና መልካም ሥራም ሳይሠሩ የእግዚአብሔር መምረጡ በምን እንደ ኾነ ይታወቅ ዘንድ። እሱ የጠራው ነው እንጂ፤ ሰው በሥራው የሚመረጥ እንዳይደለ ያውቁ ዘንድ፤ ርብቃንም ታላቁ ለታናሹ ይገዛል አላት። ያዕቆብን ወደድኹ፤ ዔሳውን ጠላኹ፤ ተብሎ እንዲኹ ተጽፏልና።" ሲል ገልጾታል። (ሮሜ ፱፡ ፱- ፲፫።) ቅዱስ ጳውሎስ በዚኽ ብቻ አልተወሰነም። በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ ሰው ሊያጕረመርም፥ ሊተች እንደማይገባው ሲያሳይ፤ **"ምንተ እንከ ንብል ይዔምፅኑ እግዚአብሔር፤ ሐሰ። ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ፤ ለዘሂ መሐርክዎ እምሕሮ፤ ወለዘሂ ተሣህልክዎ እሣህሎ። ናሁኬ ኢኮነ ለዘበደረ ወለዘሮጸ ዘእንበለ ዳእሙ ለዘእግዚአብሔር ምሕሮ። ወይቤሎ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ለፈርዖን፤ በእንተዝ አንሣእኩከ ከመ አርኢ ኀይልየ ላዕሌከ ወይሰማዕ ስምየ በኵሉ ምድር። ናሁኬ ለዘፈቀደ ይምሕር ወለዘፈቀደ የዐፅብ። ምንተ ትብል ተሐይሶኑ ለእግዚአብሔር ቦኑ ዘይትቃወማ ለምክሩ። ዕጓለ እመሕያው ምንት አንተ ዘትትዋሥኦ ለእግዚአብሔር፤ ይክልኑ ብሂሎቶ ግብር ለገባሪሁ ኢትግበረኒ ከመዝ። ኢኮነኑ ብዉሐ ለብሐዊ ይግበር እምአሐዱ ጽቡር ንዋየ መንፈቀ ለክብር ወመንፈቀ ለኀሳር።"** "እንግዲኽ ምን እንላለን፤ እግዚአብሔር ያደላልን፤ አያደላም። እግዚአብሔር ሙሴን እንዲኽ አለው፤ የምምረውን እምረዋለኹ፤ የምጠላውንም እጠላዋለኹ። አኹንም ለሮጠ፥ ለቀደመ አይደለም፤ እግዚአብሔር ይቅር ላለው ነው እንጂ። እግዚአብሔር ፈርዖንን በነገር እንዲኽ አለው፤ ስለዚኽ አነሣኹኽ፤ ኀይሌን በአንተ ላይ እገልጥ ዘንድ፤ ስሜም በምድር ኹሉ ይሰማ ዘንድ። እነሆ የወደደውን ይምራል፤ የፈቀደውንም ይቀጣል። ምን ትላለኽ፤ አንተ እግዚአብሔርን ትነቅፈዋለኽን፤ የእግዚአብሔርንስ ምክሩን የሚቃወማት አለን። ሰው ሆይ እግዚአብሔርን የምትከራከረው አንተ ምንድነኽ፤ ሥራ ሠሪውን እንዲኽ አታድርገኝ ሊለው ይችላልን። ሸክላ ሠሪ ካንድ ጭቃ ዕቃን ሊሠራ አይችልምን፤ ግማሹን ለክብር፥ ግማሹን ለኀሳር አድርጎ፤" ሲል (ሮሜ ፱፡ ፲፬- ፳፩።) የምርጫ ነገር እሱ ራሱ እግዚአብሔር በፈቀደው ብቻ እንደሚወሰን፥ የሰው ምክር፥ የሰው ምርጫ እንደማይገባበት አሳይቷል። በሌላ በኩልም፤ የዮሴፍን ድንኳን ተዋት፤ የኤፍሬምን ሕዝብ አልመረጠውም፤ የይሁዳን ሕዝብ መረጠ፤ ባርያውን ዳዊትን መረጠው፤ ባርያውን ያዕቆብን ርስቱን እስራኤልን ይጠብቅ ዘንድም በጐችን

ከሚያዋልድበት መረጠው፤ ይላል።

የምርጫ ነገር በልዩ ልዩ ክፍለ መጻሕፍት ተጽፏል። ግድ ኹሉም በደለኛ መኾን አለበት፥ ኹሉም ደግሞ ነጻ ነው ማለት አይቻልም። እንዳልነው ምርጫ የሚወሰነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነው። አማካሪ አይገባበትም። እስካኹን ያሳየነው ምርጫ እንዳለ ኾኖ ከዚኽ የበለጠ ሌላ ምርጫ እንዳለ እናሳያችኹ።

ለዚያ ምርጫ እስከ አኹን ያሳየነው የተስፋ መዝሙቻ መሥመሩ ነው። ወደ ታላቁ ምርጫ ስንገባ የምናገኘው መክፈቻ ቊልፍ፤ **“እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኀደሮ።”** “እግዚአብሔር ጽዮንን መረጣት፤ ማደሪያው ልትኾን መረጣት፤” ይላል። እንዲኹም፤ “ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች፤” ይላል። አስደናቂ ነገር ነው። ሴት ያለ ወንድ መፅነስ፤ ምድር ያለ ዘር ማብቀል። ሊቁ ያሬድ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልንና የእመቤታችንን ንግግር ባዋሐደበት መዝሙሩ፤ መልአኩ፤ “ትፀንሺአለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጂአለሽ፤” ባላት ጊዜ ድንግል የሰጠቸውን መልስ፤ **“ወትቤሎ ጠባብ እምአይቴ ረከብከ ዘከመዝ ብሥራተ ዘእንበለ ዘርዕ እምድር እትወተ ወዘእንበለ ምት እምድንግል ፅንሰተ።”** “እንዲኽ ያለውን የምስራች ከየት አገኘኸው፤ ምድር ያለ ዘር ታበቅላለች፥ ድንግል ወንድ ሳታውቅ ትፀንሳለች ማለትን ከየት አገኘኸው ብላዋለች፤” ይላል። ቅዱስ ሉቃስም፤ “ወንድ ሳላውቅ ይኽ እንዴት ይኾንልኛል፤” እንዳለችው ጠቅሶታል። ግን ኾነ። ከምርጫ ኹሉ በላይ የኾነ ምርጫ ነውና፥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና እንዳለው አደረገ። ይኽ ምርጫ ነው ወላዲተ አምላክን ከሰው ዘር ኹሉ ልዩ የሚያደርጋት፤ ተፈጥሮ አይደለም።

ወንጌላዊው ሉቃስ ስለ ብሥራት በጻፈበት ክፍል፤ ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛ ወር መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ስሟ ማርያም ወደምትባል ድንግል ተላከ ይላል። (ሉቃ፤ ፩፡ ፳፮ እና ፳፯።) ማርያም ወደምትባል ሴት አላለም። ስሙ ዮሴፍ ለተባለ ከዳዊት ወገን ለኾነ ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ስሟ ማርያም ወደሚባል፤ ይላል። ድንግል ማርያም። እመቤታችን ይኽን ስም ያገኘችው አዳም ከገነት በወጣበት ጊዜ ነው። ያሬድ፤ **“ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ።”** “ማርያም እንደ ብሩህ ዕንቊ በአዳም አካል ውስጥ ታበራ ነበር፤” ያላት ናት። ያለፈውን እንዳየን ይኽንን ከፍተኛ ምርጫ ለማየት ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንቃኝ።

ሀ፤ **“ወይቤ እግዚአብሔር አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ።”** አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ፤ “እግዚአብሔር አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ አለ።” (ዘፍ፤ ፫፡ ፳፪።)

ለ፤ **“ናሁ እፌኑ ወልድየ ፍቁርየ ወይወርድ እምሰማይ ዲበ ምድር ወይለብስ ሥጋ እምድንግል እንተ ስማ ማርያም እምዘመድከ አሐርያ ወአነጽሓ ወእሬስያ ውስተ ዘባናቲሆሙ ትውልድ ድኅረ ትውልድ እስከ ጊዜ ርደቱ ለወልድ እምሰማያት። ወውእተ ጊዜ ይከውን ቀዳሚ መድኀኒትከ ወግብአትከ ውስተ ርስትከ።”** “እነሆ ውድ ልጄን እልከዋለኹ፤ ከሰማይ ወደ ምድር ይወርዳል፤ ስሟ ማርያም ከምትባል ድንግል ሥጋን ይለብሳል፤ ከልጆችኽ እመርጣታለኹ፤ ርኵሰት የሌለባት አድርጌ እፈጥራታለኹ፤ በልጆችኽም በወገባቸው ወልድ ከሰማይ የሚወርድበት ጊዜ እስኪደርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንድትተላለፍ አደርጋለኹ። ያን ጊዜ የመጀመሪያ ድኅነትኽ፥ ወደ ርስትኽ መመለሻም ያን ጊዜ ይኾናል፤” ብሎታል። (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ።)

ሐ፤ ከገነት በወጣ በማግሥቱም የዕጣን መሥዋዕት አቅርቦ ምሕረት በጠየቀ ጊዜ ያለውን እንዲኽ ሲል ራሱ አዳም ለልጁ ለሴት በተናገረው ገልጾታል። **“አእምርኬ ዘንተ ኵሎ ወስምዐኒ ነገርየ ወለቡ ከመ ቃለ እግዚአብሔር ልዑል ይወርድ እምሰማይ ዲበ ምድር በከመ ነገረኒ ጊዜ አውፅአኒ እምውስተ ገነት። እስመ ውእቱ ይቤለኒ ከመ ቃሉ ይሰባእ በደኃሪ መዋዕል እምወለት ድንግል እንተ ስማ ማርያም ወይሜወር ውስቴታ ወይለብስ**

**ሥጋሃ ወይትወለድ በአምሳለ ሰብእ በዐቢይ ኃይል ወኪነ ጥበብ ወአልቦ ዘየአምሮ ዘእንበሌሁ ወዓዲ ለዘከሠተ ሎቱ።"** "እንግዲኽ ይኽን ኹሉ ዕወቅ፤ ነገሬን አዳምጠኝ፤ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ምድር እንደሚወርድ አስተውል፤ ከገነት ባወጣኝ ጊዜ እንደ ነገረኝ። እሱ ቃሉ በኋለኛው ዘመን ስሟ ማርያም ከምትባል ድንግል ሰው እንደሚኾን፥ በማሕፀኗ እንደሚያድር፥ ሥጋዋን እንደሚለብስ፥ በሰው አካል ባሕርይ ድንቅ ረቂቅ በኾነ ኀይሉ፥ ጥበቡ ከእሷ እንደሚወለድ ነግሮኛልና፤ ሥራውንም ከእሱ በቀር የሚያውቀው የለም፤ እሱ ከገለጠለትም በቀር።" (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ።)

መ፤ **"ወዓዲ ነገረኒ እግዚአብሔር ወይቤለኒ ኢትኅዝን ኦ አዳም እስመ ፈቀድከ ወዐለውከ ትእዛዝየ። ወናሁ እሬስየከ ወአኮ ይእዜ አላ ባሕቱ እምድኅረ ኀዳጥ መዋዕል። ወካዕበ ነገረኒ ወይቤለኒ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአውፃእኩከ እምውስተ ገነተ ትፍሥሕት ውስተ ምድር እንተ ታበቍል ሦከ ወአሜከላ ወተኀድር ውስቴታ ወአደንን ርእሰከ ወዘባነከ ወአርዕድ ብረኪከ በርስዕና ወይከውን ሥጋከ ሲሳየ ለዕፄያት። ወእምድኅረ ኀሙስ መዋዕል ወመንፈቀ መዓልት እምሕረከ ወእሣሃለከ በብዝኃ ሣህልየ ወምሕረትየ እወርድ ውስተ ቤትከ ወአኀድር ውስተ ከርሣ ለወለትከ። ወበእንቲአከ ኦ አዳም እትወለድ ከመ ሕፃን በእንቲአከ ኦ አዳም አሐውር ውስተ ምሥያጥ ወበእንቲአከ እጸውም ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ ወበእንቲአከ እትዌከፍ ጥምቀተ ወበእንቲአከ ኦ አዳም እትዌከፍ ወእትዔገሥ ሕማመ ወበእንቲአከ ኦ አዳም እሰቀል ዲበ ዕፀ መስቀል ወዝንቱ ኵሉ በእንቲአከ ኦ አዳም። ዘኵሉ ስብሐት ወእኂዝ ወዕበይ ወክብር ወሰጊድ ወዘምሮ ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ እምይእዜ ወእስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።"** "ዳግመኛም እንዲኽ ብሎ ነግሮኛል፤ አዳም! ፈቃዴን ስላፈረስክ አትዘን፤ እንድትመለስ አደርግኻለኹ፤ ግን አኹን አይደለም፤ ከጥቂት ዘመን በኋላ ነው እንጂ። ዳግመኛም እንዲኽ ብሎ ነግሮኛል፤ ተድላ ካለበት ገነት ያወጣኹኽ እኔ አምላክኽ እግዚአብሔር ነኝ። እሾኽ አሜከላ ከምታበቅልበት ምድር በውስጧ ትኖራለኽ፤ ራስኽን ዝቅ ታደርጋለኽ፤ ትጎብጣለኽ፤ በዕርግናም ጉልበትኽ ይደክማል፤ ሥጋኽም ከሞትክ በኋላ ለትሎች ምግብ ይኾናል፤ ከዐምስት ቀን ተኩል በኋላ ማለት ፭ ሺ ፭፻ ዘመን ሲፈጸም እምርኻለኹ፤ በይቅርታዬ፥ በቸርነቴ ብዛትም ይቅር እልኻለኹ፤ ወደ ቤትኽ እወርዳለኹ፤ በልጅኽ ማሕፀን ዐድራለኹ። በአንተ ምክንያት ሕፃን ኾኜ እወለዳለኹ፤ አዳም ሆይ! በአንተ ምክንያት ሰው ኾኜ ወደ ዐደባባይ እወጣለኹ፤ በአንተ ምክንያት ፵ መዓልት ፵ ሌሊት እጾማለኹ፤ በአንተ ምክንያት ጥምቀትን እቀበላለኹ፤ አዳም! በአንተ ምክንያት መከራ እቀበላለኹ፤ ግርፋቱን፥ ጦሩን፥ ችንካሩን እታገሣለኹ። አዳም! በአንተ ምክንያት በመስቀል ላይ እሰቀላለኹ፤ አዳም ሆይ! ይኽ ኹሉ የሚኾነው በአንተ ምክንያት ነው፤ ብሎ ነግሮኛል። ክብር፥ ምስጋና፥ ክብር፥ ጌትነት፥ ስግደት ከቸር አባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ክብር ይግባውና ይኽን ኹሉ ነግሮኛል።" (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ።) ይኽ ከዚኽ በላይ የዘረዘርነው ጌታ ከአዳም ጋር የተነጋገረው ቃል ሲኾን አዳምም በመጨረሻ ሕይወቱ ለልጁ ለሴት ለልጅ ልጆቹም በቃልም በጽሑፍም ያስተላለፈው ነው።

ሠ፤ **"ወአነ እትቀነይ ለውእቱ ብእሲ ወይሰመይ ስሙ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ወይሰቀል ዲበ ዕፅ ወያአትት መርገመ።"** "እኔ ለዚያ ሰው እገዛለኹ፤ ስሙ ወልደ እግዚአብሔር ይባላል፤ በመስቀል ላይ ይሰቀላል፤ መርገምን ያርቃል።" ይኽ ቃል ካህኑ መልከ ጼዴቅ ከይስሐቅ ሚስት ከያዕቆብ እናት ከርብቃ ጋር በተነጋገረበት ጊዜ ስለ ያዕቆብ የተነበየው ነው። (መጽሓፈ ቀሌምንጦስ።)

በዚኽ መሠረትም ነቢዩ ዳዊት ስለ ጌታ በተናገረው በመዝሙር ፻፱፤ **"መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሕ፤ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ።"** "እግዚአብሔር ማለ፤ አይጠጠትም፤ እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት የዓለም ካህን አንተ ነኽ፤" ብሎታል።

ረ፤ **"ወረከበ መካነ ወቤተ ህየ እስመ ዐርበት ፀሓይ ወነሥአ እምውእቱ እብን ዘውስተ ውእቱ ብሔር ወወደየ ውስተ ትርአሲሁ ወሰከበ በውእቱ መካን። ወሐለመ ወይሬኢ ሰዋስወ ዘወርቅ ውስተ ምድር ወርእሱ ይጐድእ ሰማየ ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ ቦቱ ወእግዚአብሔር ይቀውም ላዕሌሁ። ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ አቡከ ኢትፍራህ ዛተኒ ምድረ እንተ ውስቴታ ትሰክብ ለከ እሁበከ ወለዘርዕከ። ወይከውን ዘርዕከ ከመ ኆፃ ባሕር ወይበዝኅ ወይመልእ እስከ ባሕር ወውስተ አዜብ ወመስዕ ወውስተ ጽባሕ ወይትባረኩ ብከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ወበዘርዕከ። ወአነ አሐውር ምስሌከ ወአዐቅበከ በኵሉ ፍኖትከ እንተ ተሐውር ወአገብአከ ውስተ ውእቱ ምድር ወኢየኀድገከ እስከ እገብር ለከ ኵሎ ዘእቤለከ። ወነቅሐ ያዕቆብ እምንዋሙ ወይቤ እግዚአብሔር ሀሎ ውስተ ዛቲ ምድር ወአንሰ ኢያእመርኩ። ወፈርሀ ወይቤ ግሩም ውእቱ ዝንቱ ምድር ወይከውን ዝየ ቤተ እግዚአብሔር ወዛቲ ይእቲ ኆኅታ ለሰማይ።"** "ፀሓይ በጠለቀች ጊዜም ያዕቆብ ከመንገዱ ወጣ ብሎ ባገኘው ቦታ ላይ ዐደረ፤ በዚያ ስፍራ ካገኛቸው ድንጋዮች ወስዶ ከትራሱ በታች አድርጐ ተንተርሶ በዚያ ቦታ ተኛ። ሕልም አለመ፤ ከምድር እስከ ሰማይ የደረሰ የወርቅ መሰላል ያያል፤ (ቀሌምንጦስ ሰዋስው ዘእሳት ይላል። ልዩ ምስጢር የተፈጸመበት መኾኑን ያሳያል።) የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር፤ እግዚአብሔር በላዩ ተቀምጦ ነበር። እግዚአብሔርም የአብርሃም፥ የአባትኽ የይስሐቅም አምላክ እኔ ነኝ፤ አትፍራ፤ ይኽችን የተኛኽባትን ምድርም ለአንተ፥ ከአንተም በኋላ ለዘርኽ እሰጣታለኹ። ዘርኽ እንደ ባሕር አሸዋ ይኾናል፤ ይበዛል፤ በምድር ላይም በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ይመላል፤ የምድር አሕዛብ ኹሉ በአንተ፥ በዘርኽም ይባረካሉ። እኔ ከአንተ ጋራ እኖራለኹ፤ በምትኼድበት መንገድ፥ በምትኖርበት ዘመን ኹሉ እጠብቅኽአለኹ፤ ወደዚኽ ምድር እመልስኻለኹ፤ የነገርኩኽን እስካደርግልኽ ድረስ አልለይኽም አለው። ያዕቆብ ከዕንቅልፉ ነቃ፤ እኔ አላውቅኹም እንጂ እግዚአብሔር በዚኽች አገር አለ አለ። ፈራ፤ ይኽ ቦታ የሚያስፈራ ነው፤ ከዚኽ ቤተ እግዚአብሔር ይሠራል፤ ይኽች የሰማይ በር ናት አለ።" (ዘፍ፤ ፳፰፡ ፲፩- ፲፯።) ይኽን ሙሴ በኦሪት ዘፍጥረት የገለጸውን ቅዱስ ቀሌምንጦስ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳስተማረው በመጽሐፉ ጠቅሶታል። "በዘርኽ አሕዛብ ይባረካሉ፤" የሚለው ቃልም እግዚአብሔር ቃል ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው የኾነላትን ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክን፤ እንዲኹም ሰው የኾነውን አምላክ፥ ወልደ አምላክ ልጇን ያመለክታል። ሙሴ፤ "ሰዋስው ዘወርቅ፤" "የወርቅ መሰላል፤" ብሎአል። ንጽሕናዋን፥ ቅድስናዋን ያመለክታል። ቀሌምንጦስ፤ "ሰዋስው ዘእሳት፤" ይላል። የእሳተ መለኮት ማደሪያ መኾኗን ያመለክታል።

ይኽንንም ቅዱስ ጴጥሮስ ለደቀ መዝሙሩ ለቀሌምንጦስ ጌታ የነገረውን እንዲኽ ሲል ገልጾታል። **"ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢተሰባእኩ እምኢተፈጥረ ዓለም። ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢተሠገውኩ እማርያም ቅድስት እምኢፈጠርክዎ ለአዳም ወኢለሰማያት ወለምድር፤ ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢተሰባእኩ እምኢተዓውቀ ብዕለ ክብርየ ወስብሐትየ። ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢያፍቀርኩከ እምኢከሠትኩ ለከ ዘንተ ምስጢረ ወናሁ እከሥት ለከ። ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢያፍቀርክዎ ለሰብእ እምኢያስተርአይክዎሙ በዝንቱ ሥጋ፤ ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢኮነት ዛቲ ቅድስት ድንግል እምኢፈጠርክዋ ለሔዋን።"** "ጴጥሮስ ሆይ! ሰው የማልኾን ቢኾን ኖሮ ዓለም ባልተፈጠረ ነበር። ጴጥሮስ! ከቅድስት ማርያም ሥጋን የማልነሣ ቢኾን ኖሮ አዳምን፥ ሰማይንም፥ ምድርንም ባልፈጠርኳቸው ነበር። ጴጥሮስ! ሰው ባልኾን ኖሮ ክብሬ፥ ጌትነቴ ባልተገለጠ ነበር። ጴጥሮስ! ባልመርጥኽ ኖሮ ይኽን ምስጢር ባልገለጽኩልኽ ነበር፤ ሌላውንም እገልጽልኻለኹ። ጴጥሮስ! ሰውን ባልወደው፥ ባልመርጠው ኖሮ በዚኽ አካል ባልተገለጽኩላቸው ነበር። ጴጥሮስ! ይኽቺ ቅድስት ድንግል ባትኾን፥ እሷ ባትፈጠር ኖሮ ሔዋንን ባልፈጠርኳት ነበር፤" እንዳለው ገልጾአል። በደብረ ዘይት በዚያ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ የተገኙት ሦስቱ

ምስክሮች ጴጥሮስ፥ ያዕቆብ፥ ዮሐንስና ልዕልናዋን፥ ክብሯን የሚገልጽላቸው እናቱ ብቻ ስለ ነበሩ፤ **"ሶበሰ ኢኮነት ዛቲ ቅድስት ድንግል እምኢፈጠርክዋ ለሔዋን፤"** "ይኽቺ ቅድስት ድንግል ባትኾን ኖሮ፥ እሷ የማትፈጠር ቢኾን ኖሮ ሔዋንን ባልፈጠርኳት ነበር፤" ብሎ የቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክ የክብር፥ የልዕልና ምርጫ ጥንቱን በአምላክ ዐሳብ የተወሰነ መኾኑን ገልጾ ምእመናን ልጆቹ፥ እናታቸው ቤተ ክርስቲያንም በዚኹ መዓርግ እንዲያውቋት፥ እንዳይጋፉ፥ እንዳይዳፈሩ ኀያል አምላክ ልጇ መልእክቱን አስተላልፏል።

እንግዲኽ መልአኩ ገብርኤል ይኽችን ቅድስት ድንግል ለመፈለግ ነው ወደ ናዝሬት፥ ወደ ገሊላ፥ ወደ ዮሴፍ ቤት የኼደ። በዘር፥ በሩካቤ መወለድ በረከት ስለ ኾነ ከአዳም እስከ ዕለተ ምጽአት በሰው ዘር ሐረግ ጸንቶ የሚኖር ሲኾን፤ በዘር፥ በሩካቤ ተወልዶ ያለ ዘር፥ ያለ ሩካቤ በድንግልና መውለድ ግን የተሰጠ ለአንዲቱ ቅድስት ድንግል ለሷ ብቻ ሲኾን፤ ያለ ዘር፥ ያለ ሩካቤ መወለድም የልጇ ገንዘብ ብቻ ነው። ስለዚኽ የቀደሙ አበው ይኽን ትምህርት፥ እምነት ጠንቅቀው አስተላልፈውልናል። ነቢያት በትንቢታቸው፥ ሐዋርያት በስብከታቸው፥ ሊቃውንትም በመጻሕፍቶቻቸው ይኽን የሚጋፋ አልጻፉም።

በዚኽ መጽሐፍ የገለጽኩላችኹ ኹሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸ ነው። ትርፍ አልጨመርኩም። ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ያለው በነቢያት መጻሕፍት፥ ከዚያ ወዲኽ ያለው ደግሞ በሐዋርያት፥ በሊቃውንት መጻሕፍት ተገልጸአል።

ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ፤ **"ነዋ ወልድኪ ወነያ እምከ።"** "እነሆ ልጅሽ፤ እንኋት እናትኽ፤" ሲል ከተናገረበት ሰዓት ጀምሮ ደግሞ እስከ ዕለተ ምጽአት ቤተ ክርርቲያን እመ አምላክን ቅድስት ድንግል እመ አምላክ፥ ወላዲተ አምላክ እያለች ታመሰግናለች። ከዚኽም ጋራ በግንዘቱ ጊዜ፤ "**ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ። ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ዘተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ። ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ተሣሃለነ እግዚኦ**።" "ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ የማይሞት ሕያው፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ፤ አቤት ይቅር በለን። ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ የማይሞት ሕያው፤ በዮርዳኖስ የተጠመቀ፤ በዕፀ መስቀል ላይ የተሰቀለ፤ አቤት ይቅር በለን። ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ የማይሞት ሕያው፤ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፤ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ያረገ፤ በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ፤ ዳግመኛ በሙታን በሕያዋን ሊፈርድ በክብር በጌትነት የሚመጣ፤ አቤቱ ይቅር በለን፤" እያለች ቤተ ክርስቲያን እንድታመሰግነው ትእዛዝ ሰጥቷል። በእነዚህ ተወልደ፥ ተጠምቀ፥ ተሰቅለ፥ ተንሥአ፥ ዐርገ፥ ነበረ፥ ዳግመ ይመጽእ በሚሉት ሰባት ቃላት ምስጢረ ሥጋዌን አጠቃሎ ለቤተ ክርሰቲያን ሲያስተላልፍ ይህ ምስጢር በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ላይ በተፈጸመው ጥልቅ ረቂቅ ሥራው እንደ ተከናወነ ገልጾ ትእዛዙን አስተላልፎልናል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ስፍራ ሁሉ ጧትና ማታ ይህ ኪዳን ይደረሳል፤ ይነገራል። እንግዲህ ስለ ወላዲተ አምላክ የምንማረው፥ የምናስተምረው፥ የምንመሰክረው ሁሉ በገነት በተስፋ ቃል ኪዳን ንግግር ተጀምሮ በቀራንዮ፥ በጎልጎታ የተፈጸመ ወደ ፊትም በዕለተ ምጽአት የሚታተም ነው። ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከዚህ አትለፉ፤ ከዚህ አትትረፉ። በዚህ ጽኑ፤ ተወሰኑ። ከዚህ በፊት የበደላችሁ ተመለሱ፤ ንስሐ ግቡ። ያልገባችሁ ተጠንቀቁ። ከአባቶቻችሁ የወረሳችሁትን ትምህርት ብቻ ጠብቁ።

በተለይ ኢትዮጵያውያን አበው ሊቃውንቱ ብቻ ሳይኾኑ ነገሥታቱ ሳይቀሩ በሷ ስም፥ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እነ ቅዱስ ያሬድ፥ እነ አባ ጊዮርጊስ፥ እነ አባ ጽጌ ድንግል፥ እነ ዐፄ

ዘርዓ ያዕቆብ፥ እነ ዐፄ ናዖድ፥ እነ ዐፄ ልብነ ድንግል የደረሷቸው የምስጋና መጻሕፍት ብዙዎች ናቸው።

በዜና ልደታ ጋዜጣ ላይ የወጣው ጽሑፍ ጸሓፊ ስለዚኽ መጽሐፍ አልተጻፈልንም ሲል አስደንቆኛል።

እንግዲኽ እኔ ይኽን መጽሓፍ የማዘጋጀው፥ ሌሎችንም ከዚኽ በፊት የታተሙትን፥ ወደ ፊት የሚታተሙትንም ያዘጋጀኋቸው በዕውቀት ከሌሎች እበልጣለኹ ብዬ አይደለም። እኛ ኢትዮጵያውያን ነውር ነቀፋ የሌለባት የቀናችውን የእግዚአብሔር መንገድ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ጠንቅቃ ጠብቃ የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ከኾንን እንደ እናታችን እንድንኾን እንጂ ያልዘሩ በቀል እንዳንኾን ለማስጠንቀቅ ነው። እኔ እንደ አባቶቼ፤ **“ኦ ቡርክት እምኵሉ ፍጥረት አንቲ ውእቱ ህየንተ አርያም ዘበሰማያት ዘኮንኪ አርያመ በዲበ ምድር። ብኪ አስተማሰሉ ቅዱሳን ነቢያት ካህናት ወነገሥት ገብሩ ሎሙ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን።”** “ከፍጥረት ኹሉ የከበርሽ መርገመ ሥጋ፥ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፤ በረከተ ሥጋ፥ በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጪ፥ የምታድዪ እመቤቴ! በሰማይ ባለችው ጽርሐ አርያም ፈንታ በምድር ላይ ጽርሐ አርያም ኾነሻል። ቅዱሳን ነቢያት፥ ካህናት፥ ነገሥታት አንቺን አስመስለው፥ በአንቺ ምሳሌ አድርገው ቅድስተ ቅዱሳንን አዘጋጅተው በውስጧ ጽላተ ኪዳንን አኑረዋል።” አንቺም ምሳሌው የውጣ የኾነለት የአካላዊ ቃል እናቱ ነሽና እንደ አባቶቼ ንጽሕናሽን፥ ቅድስናሽን፥ ድንግልናሽን፥ ክብርሽን፥ ልዕልናሽን አምናለኹ፤ አስተምራለኹ። የሚከተለኝ ኹሉ ጥሪዬን እንዲሰማ አውጃለኹ።

ከመጻሕፍት ቃል ዐልፋችኹ፥ ተርፋችኹ፤ “ጥንተ አብሶ አለባት፥ በዘር፥ በሩካቤ የተወለደች ናት፥ ሰው ናትና ከሰማይ የመጣች አይደለችም፤” እያላችኹ የምትቱ ኹሉ፤ ወይም እንደ እነ እገሌ መኾን አለብን የምትሉ ኹሉ ልባችኹን እዘዙ። እንደበታችኹን ግዙ። ከትዕቢት አትለፉ። ንስሐ ግቡ።

በተለይ ወንድሜ ንቡረ እድ ቄስ ኤርምያስ፤ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ናት በሚል አነጋገር የሚነዙትን ትምህርት፤ ከዚያም ዐልፎ ሰባቱ ኪዳናት በማለት የሚነዙትን አሉባልታ፥ ስሕተት ቢያርሙ መልካም ነው። የምመክርዎ እንደ ወንድምነቴ ነው። የአምላክ እናት ግዑዝ ፍጥረት አይደለችም። ኢትዮጵያም ሰው አይደለችም፤ አገር ናት። ድንግል ማርያም ቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ ናት። ኢትዮጵያ ደግሞ የእግዚአብሔር አገር ናት፤ ለእናቱም በቃል ኪዳን የሰጣት ርስቷ ናት። ይኼ ነው ኹሉም ሊያውቀው የሚገባው።

ምእመናን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ኹሉ! አባቶቻችኹ ጌታንም፥ እመቤታችንንም በመናቅ፥ በመሳደብ በደል ያልሠሩ ንጹሐን፥ ቅዱሳን ስለ ኾኑ እናንተም ጊዜ የወለዳቸውን መናፍቃን ሳትከተሉ እምነታችኹን ጠብቃችኹ፥ ከኑፋቄ ርቃችኹ እንድትኖሩ ይኽን መጽሐፍ አዘጋጅቼላችኹአለኹ።

እመቤታችን በሥነ ፍጥረት በአምላክ ቸርነት ታስባ ተመርጣ ከአዳም ጀምሮ እስከ ወላጆቿ ድረስ በንጹሕ ዘርነት በአባቶቿ ወገብ ተቋጥራ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈች ልጇ ከሰማይ ወደ ምድር የሚወርድበት፥ ከሷ ሥጋን፥ ነፍስን ነሥቶ በነሣው አካል ባሕርይ መከራ መስቀልን ተቀብሎ አዳምንና ልጆቹን የሚያድንበት ሰዓት እስኪደርስ በ፳፮ቱ ትውልደ አበው እየተላለፈች እዚኽ የደረሰች መኾኗን፤ ከዚያ በኋላም የተመረጠችበትን ክብር አግኝታ የአምላክ እናት ኾና ከፍጥረት ኹሉ በላይ በኾነ የክብር፥ የቅድስና፥ የልዕልና መዓርግ እስከ ዕለተ ምጽአት ስትመሰገን የምትኖር መኾኗን፤ በመንግሥተ ሰማያትም ምስጋና የማይቋረጥባት መኾኗን ቅዱሳን መጻሕፍትን መሠረት አድርጌ ያዘጋጀኹላችኹን ይኽን መጽሐፍ ተቀብላችኹ እንድትጠቀሙበት ዐደራ እላለኹ።

# ማጠቃለያና ምክር።

## ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር።

(መዝ፤ ፹፮፡ ፫።)

የተወደዳችኹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን! ከኹሉ አስቀድሞ ለምንሠራው ሥራ ኹሉ ራሳችንን፥ ዐቅማችንን ማወቅ፥ ከእግዚአብሔር የተሰጠንን መምሪያ መጠበቅ፥ ረድኤቱን አጋዥ ማድረግ እንደሚገባን ላሳስብ እወዳለኹ። ሰው ምንም በተሰጠው አእምሮ ራሱን መምራት የሚችል ኾኖ ቢፈጠርም ብዙ ስለሚጐድለው እግዚአብሔርን መሪ አድርጎ መንቀሳቀስ ይገባዋል። ከሰው ሊገኝ የሚችል ነገር ቢኖር ጥቂት ነው። አብዛኛውም ክፉ ነው። ስለዚኽ እጅግ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ የሃይማኖት ጉዳይ ላይ። በመጽሐፍ የተገለጠው አንድ ሃይማኖት፥ አንድ ጥምቀት፥ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ግን ሰዎች በየጊዜው በከፈቱት መንገድ ኹሉም ነገር ጠፍቷል። የእግዚአብሔር መንገድ የቀናች ትኹን እንጂ በሯ ጠባብ ነው። መንገዲቱም አስጨናቂ ናት። በማስተዋል ካልኾነ በዘፈቀደ የሚንቀሳቀሱባት አይደለችም። ይኽ ስለ ኾነ ነው ማለት ማስተዋል ከሰዎች ዘንድ ስለ ጠፋ ነው እግዚአብሔር በደሙ የዋጃት ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ገጽ ለመጥፋት የደረሰችው። የዓለም ቤተ ክርስቲያን ለመባል የበቃችው። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መኾኗ ቀርቶ ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ፤ ለመንጋውና ለራሳችኹ ተጠንቀቁ፤ ሲል መልእክት አስተላልፎ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሹማምንት ግን ይኽን መልእክት ችላ ስላሉት ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ሳይቀር ለመጥፋት በቃች። ከኹሉ በላይ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሎ የተነገረላት አገር እጆቿን ከእግዚአብሔር መልሳ ወደ ልዩ ልዩ ሰዎች በመዘርጋቷ አሳዛኝ ኹኔታ ላይ ደርሳለች። ስሟ እስከ መጥፋት ደርሷል። ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ በሕገ ልቡና በመጽሐፈ ሔኖክ፥ በሕገ ኦሪት በኦሪትና በነቢያት መጻሕፍት፥ በዘመነ ሐዲስም በጌታችን ትምህርትና በሐዋርያት መጻሕፍት ተጠብቃ የኖረች አገር ዛሬ በኹሉም ተራቁታ ትገኛለች። ጌታ በዕለተ ስቅለት እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ፥ ደቀ መዝሙሩንም ለእናቱ ዐደራ ከማለቱ አስቀድሞ በስደቱ ሕዝቧን ዐሥራት፥ አገሪቱን ርስት አድርጌ ሰጥቼሻለኹ ብሎ ኢትዮጵያን ለእናቱ የዐደራ ርስት፥ ሕዝቧን የዐደራ ልጆች አድርጓል። ይኸም፤ እምነ ጽዮን ብሎ ለመጥራት ለታደሉት ለተስፋ ልጅነታቸው ፍጻሜ ነበር። ስለዚኽም ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ብቻ ሳይኾኑ ሕዝቡም ጭምር እመቤታችንን በልዩ ይወድ፥ ያከብር፤ ድንግልናዋን፥ ቅድስናዋን፥ ከፍጥረት ኹሉ በላይ ያለ ልዕልናዋን ያምን ነበር። አንድም የሚጠራጠር አልነበረም። የፕሮቴስታንት ልዩ ልዩ ረድፈኞች ከገቡ በኋላ ግን ያ ኹሉ ነገር ቀርቶ አክብሮቱ ወደ ነቀፋ፥ ምስጋናው ወደ ስድብ ዞሯል። የውጭ ጥገኞች ከኾኑትም ይልቅ ስማቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኾኖ በእመቤታችን ክብር፥ ልዕልና፥ ቅድስና ላይ ብዙ የዐመፅ ቃል የሚናገሩ፥ የሚጽፉ ቍጥራቸው እየጨመረ ኼዷል። ይኸም ዲያቆናት፥ ቀሳውስት፥ ጳጳሳት እንከሚባሉት ደርሷል። በእነ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፥ በእነ ጽጌ ስጦታው፥ በእነ ቄስ አስተርአየና በጉባኤው፥ በዜና ልደታ ጋዜጣ ላይ የወጣው ጽሑፍ ጸሐፊ በጽሑፍ ተገልጦ፥ በቃል ተላልፎ በማግኘቴ በጣም አዝናለኹ። ይልቁንም እነ ቄስ አስተርአየ፥ እነ ዲያቆን ጽጌ ከእኔ ጋር እንደ ተነጋገሩ አስመስለው በመጻፋቸው ተገርሜአለኹ። ነገሩ አላስደነቀኝም። ቅዱስ ጳውሎስ፤ እሱ ራሱ ሰይጣን መልአከ ብርሃን መስሎ ይመጣልና ሐዋርያቱም የክርስቶስን ሐዋርያት መስለው ይመጣሉ፤ ብሏልና። (፪ ቆሮ፤ ፲፩፡ ፲፬።) ስለዚኽ፤ **“እስመ ለሊሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመ መልአከ ብርሃን (አስተርአየ)፤”** ማለቱ ነው መሰለኝ። እኔ ግን ከእነሱ ጋር ግንኙነትም ንግግርም የለኝም። ምእመናን ይኽን እንድታውቁልኝ እፈልጋለኹ። በዜና ልደታ ጋዜጣ ላይ

የወጣው ጽሑፍ ጸሓፊ ደግሞ፤ በስልክ ደውለው ሲያነጋግሩኝ፤ ምነው እንዲኽ ኾነ፤ ብላቸው፤ በኢትዮጵያ ስለ እመቤታችን የተጻፈ የለም ነው ያሉኝ። ከኾነልኽ አንተ ጻፍ አሉኝ። እኔም በነገሩ ተገርሜ ሳልቀር መልሱን ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን የቅድስተ ቅዱሳን ዜና ሕይወት፤ ከገነት እስከ በረት፥ ከቀራንዮ እስከ መንግሥተ ሰማያት፥ ከዕለተ ፍጥረት እስከ ዕለተ ስቅለት፥ ዕለተ ትንሣኤና ዕለተ ዕርገት፤ ወይም ግንቦት፥ ልደታና ዕርገት በሚል አርእስተ ነገር ተነሥቼ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ወላዲተ አምላክ ማርያም ይኽን መጽሐፍ አዘጋጅቼ አሳትሜላችኹአለኹ።

ባዕድ፥ የውጭ ቃል አልጨመርኩም። የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ብቻ ነው። የሚገርመው በዝግጅቱ ጊዜ ባጋጠመኝ ችግር የተደረገልኝ የወላዲተ አምላክና የልጇ ተአምራት ነው። በአኹኑ ጊዜ የእኔን ሕይወት በቅርብ ያለ ኹሉ የሚያውቀው ሲኾን እንኳን ወደ ሌላ ቦታ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኳ መንቀሳቀስ የማልችል የክርስቶስ የኹለት ጊዜ የቤት እስረኛ ነኝ። በዚኽ ምክንያትም እንኳን በሩቅ ያሉ መጻሕፍትን እርዳታ እንደ ልብ ላገኝ በቅርብ ላሉትም ዐቅም ያጥረኛል። ልጆቼ ወደ ትምህርት ቤት ከኼዱ፥ ለመልእክት ከወጡ ችግሬን ማቃናት አልችልም። ከዚያ ይበልጥ ደግሞ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚታመኑ በ፹፩ መጻሕፍት ቍጥር ውስጥ ያሉ ታላላቅ መጻሕፍት ያልታተሙ በመኾናቸው ምክንያት በየቤተ ክርስቲያኑ አይገኙም። ይልቁንም ጌታ፤ ከልጅ ልጅኽ ተወልጄ አድንኻለኹ፤ ሲል ለአዳም የሰጠው የቃል ኪዳን ቃል የሚገኘው በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ስለ ኾነ፤ ከዚኽም ጋራ ስለ እመቤታችን ዜና ሕይወት ብዙ ቃላትን የያዘ ይኸው መጽሐፍ በመኾኑ ይኽን መጽሐፍ ለማግኘት በእኔ ላይ የነበረው ችግር ሊነገር የማይቻል ነበር። ይኽ መጽሐፍ ያስፈለገኝ በቅርብ ካሉኝ መጻሕፍት ጋራ፤ "እሷ ሰው ናት፥ ከሰማይ የወረደች አይደለችም፤ ከጥንተ አብሶ፥ ከመርገም፥ ከበደል ነጻ አይደለችም፤ ከበደለኞች መኻከል ናት፤ **"ወባሕቱ ኰነኖሙ ዳእሙ ሞት እምአዳም እስከ ሙሴ ለእለሂ አበሱ ወለእለሂ ኢአበሱ በእንተ ይእቲ ኃጢአቱ ለአዳም እስመ ዅሉ በአምሳለ አዳም ተፈጥረ።"** "ነገር ግን በዚች በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከአዳም እስከ ሙሴ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው፤ ኹሉ በአዳም አምሳል ተፈጥሯልና፤" **"ወሶበ አለውነ ትእዛዞ በምክረ ከይሲ ርጉም ወፃእነ እምገነተ ተድላ ውስተ ሙስና።"** "በርጉም ከይሲ ምክር ትእዛዙን ባፈረስን ጊዜ ከተድላ ገነት ወደ ጥፋት ወጣን፤"" የሚሉትን ቃላት በመጥቀስ ቅድስተ ቅዱሳንን የእነሱ ማኅበረተኛ ለማድረግ ሽንጣቸውን ገትረው የሚሟገቱትን ለማሳፈር ስለ እመቤታችን ዜና ሕይወት ብጥር ንጥር ያሉ ቃላትን መምረጥ ስለ ነበረብኝ ነው።

የእመቤታችን ዜና ሕይወት ከአዳም ተፈጥሮ ጀምሮ ቅድስት ድንግል በልደተ ሥጋ ከሐና ከኢያቄም እስከ ተገኘችበት ጊዜ ድረስ ለእሷ የተመደበው በእግዚአብሔር ሥልጣን የታቀደው የተስፋ መሥመር ልዩ፥ ማንም የማይቀላቀልበት፥ ያልተቀላቀለበት መኾኑን ለማሳየት ትግል ማድረግ ነበረብኝ። ለዚኽም መጻሕፍትን ኹሉ መዳሰስ ነበረብኝ። በዚኽ ጊዜ ነው የእግዚአብሔር ተአምራቱ የተገለጸው። ዘወትር ከማነበንበው መዝሙረ ዳዊት፤ **"መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን፤" "መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ላይ ናቸው።" "ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር።"** "የእግዚአብሔር አገር ሆይ! እግዚአብሔር ስለ አንቺ የተናገረው፥ ያናገረው ነገሩ ልዩ ነው፤" የሚሉትን ቃላት መጫሪያ፥ መቈፈሪያ አድርጌ ወደ ገነት፥ ወደ ዕለተ ፍጥረት የዳሰሳ ጉዞዬን ቀጠልኩ። በዚያም፤ "አዳም ከኛ እንደ አንዱ ኾነ፤" የሚለውን ቃል ተመርኩዤ ቆም ብዬ ሳሰላስል፤ "ከልጅ ልጅኽ ተወልጄ አድንኻለኹ፤" የሚለው ቃል ትዝ አለኝ። አበው ይኽ ቃል የሚገኘው በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ነው ሲሉ ሰምቼአለኹ። ይኽን መጽሐፍ ቀደም ሲል ባገሬ በዲማ፥ እዚኽም ከመጣኹ በቤተ ክህነት እሥራ ላይ በነበርኩበት ጊዜ ከግቢ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ለሥራ በትውስት መጥቶ አይቼዋለኹ። ግን እንደ አኹኑ ባላጋራ አልተነሣም ነበርና ያን ጊዜ በጉዳዩ አላተኰርኩበትም ነበር። አኹን ግን፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ነን ባዮች ዐዲስ ሰልፍ ሠርተው ተነሥተው የወላዲተ

አምላክን ልዕልና የሚጋፉበት ጊዜ ስለ መጣ ዐዲስ ጉልበት አስፈለገኝ። ለዚኽም ምንም ብዙ መጻሕፍት፥ ብዙ መረጃዎች አጠገቤ ቢኖሩም የቅዱስ ቀሌምንጦስ ቃላት ያስፈልጉኝ ነበር። ግን መጽሐፉን የት ላግኘው? በዚኽ ጊዜ ሥራ የማይሳነው እግዚአብሔር ልጁ በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ የነበረውን ሰው እንዳሰበው፥ ስንቁንም በዚያው ባለበት እንደ ሰጠው፤ እኔንም በዚችው በታሰርኩባት ክፍሌ ዐሰበኝ። ያን የፈለግኹትን መጽሐፍ በልዩ ክቡር መልእክተኛው እጅ እቤቴ ድረስ ላከልኝ። በላኹት። የምጠግብ አልመሰለኝም ነበር። ግን ልጨርሰው አልቻልኩም። ማንም ሰው ቢበላው ቢበላው የሚያልቅ አይደለም። ኾኖም ለእኔ የሚኾነኝን ከቀመስኩ፥ ካሸተትኩ በኋላ ለእናንተም የሚኾነውን ከሌሎቹ መጻሕፍት ጋር አዋሕጄ በዚች መጽሐፍ አስተላልፌላችኋለኹ። ነቢዩ ዳዊት፤ "ጠዓሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር።" "እግዚአብሔር ቸር ችንደ ኾነ ቅመሱና ዕወቁ፤" ይላል። ስለዚኽ ዕፁብ ድንቅ ተአምራቱን ከነገርኳችኹ ከቃላቱ በመጽሐፉ ውስጥ ያሰፈርኳቸውን አንብባችኹ እንድትረዱ ዐደራ እላለኹ።

በሙሴ ድንኳን ዐሥሩ ክንድ፥ ሰሎሞን በሠራው ቤተ መቅደስ ኻያው ክንድ ተለይተው ቅድስተ ቅዱሳን ይባሉ ነበር። ልዩነታቸው ይኼ ነው። እመቤታችንም በተፈጥሮ ሰው፥ የሰው ልጅ ትኹን እንጂ ልዑል አምላክ ልጁ ቅድስተ ቅዱሳን የራሱ ማደሪያ አድርጐ ስለ ፈጠራት በምንም በምንም ከሰው ጋር የምትቀላቀል አይደለችም። ስለዚኽም ገና ከመጀመሪያው፤ ቅድስት ድንግል ማርያም የሚለው ስሟ በግል የወጣላት ነው። ቀጥሎም በንጹሕ ዘርነት በአበው ወገብ ተቋጥራ ወልድ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድበት፥ ከሷ ሥጋ የሚለብስበት ጊዜ እስኪደርስ በአበው ወገብ ከትውልድ ወደ ትውልድ በልዩ መሥመር ስትተላለፍ የኖረች ናት። ስለዚኽም እግዚአብሔር ለአዳም በነገረው ቃል፤ **"አሐርያ ወእሬስያ ውስተ ዘባናቲሆሙ ትውልድ ድኅረ ትውልድ እስከ ጊዜ ርደቱ ለወልድ እምሰማያት።"** "እመርጣታለኹ፤ ወልድ ከሰማይ እስኪሚወርድበት ጊዜ ድረስም ከትውልድ ወደ ትውልድ በአበው ወገብ እንድትተላለፍ አደርጋታለኹ፤" ብሎታል። ይኽንን ይዞ ነው ነቢዩ ዳዊት፤ መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ላይ ናቸው፤ የእግዚአብሔር አገር ሆይ! እግዚአብሔር ስላንቺ የተናገረው ነገሩ ልዩ ነው፤ ያለው። አዳም፥ ሴት፥ ኖኅ፥ ሴም፥ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ፥ ዳዊት፥ ማትያን፥ ቅስራ፥ ኢያቄም፤ እነዚኽ አበው ለተስፋው መሥመር የተፈጠሩ ልዩ መሥመሮች ናቸው። ፷፯ ተውልደ አበው። ይኽንን ነው ጌታ፤ ስሟ ማርያም ከምትባል ቅድስት ድንግል ልጅኽ ተወልጄ አድንኻለኹ፤ እመርጣታለኹ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ በአበው ወገብ እንድትተላለፍ አደርጋታለኹ፤ ያለው ስለዚኽ ነው። ከገነት እስከ በረት፥ ከዕለተ ፍጥረት እስከ ዕለተ ልደት በተስፋ ምስጢር መሥመር ተጠብቆ የኖረው የአምላክ ሥራ በተመደበላት ጊዜ እሷ ስትመጣ ተጀምሮ ልጁ በልደቱ፥ በጥምቀቱ፥ በስቅለቱ፥ በሞቱ፥ በትንሣኤው፥ በዕርገቱ በፈጸመው ሥራና ኀይል ትምህርት ተአምራት ተገልጧል።

የሚገርማችኹ ነገር ቢኖር መሠረተ ሕይወት፥ ተፍጻሜተ መድኀኒት ቅድስት ድንግል የተወለደችበት፥ በሷ ላይ የተጀመረው የቸርነት ሥራ የተፈጸመበት ወር ግንቦት መኾኑ ነው። ግንቦት፤ ልደታ፥ ዕርገትና ርደተ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት (በሐዋርያት ላይ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ)።

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፱ ከቊጥር ፲፫ እስከ ፲፯ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋራ ቃል ኪዳን ማድረጉ ተገልጾአል። ቀስቱ በደመና ላይ በሚሣልበት ጊዜ ደጋኑ ወደ እሱ፤ ወተሩ፥ ገመዱ ወደ ፍጥረቱ ኾኖ ይገኛል። ወተሩ የደጋኑን ጫፍና ጫፍ ይነካል። ደመናው የሰው ሕይወት፥ ደጋኑ የእግዚአብሔር ምሕረት፥ ወተሩ ከመጀመሪያ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሐና፥ ኢያቄም የደረሰው የቅድስተ ቅዱሳን ዜና ሕይወት ነው። ኖኅ ይኽን ቃል ኪዳን የተቀበለው ወደ መርከብ በገባበት፥ ኋላም ከመርከብ በወጣበት በግንቦት ወር ነው። ይኽም በመኾኑ ከአዳም እስከ እሷ የተዘረጋው የተስፋ መሥመር እስከ እሷ ሲደርስ ቅድስት ድንግል ግንቦት ፩ ቀን ተወለደች። ሲጠበቅ ቈይቶ በሷ ሊፈጸም የታቀደው የእግዚአብሔር የቤዛነቱ ሥራም በዕርገትና በርደተ መንፈስ ቅዱስ

ሲከናወን የሰውን አካል ባሕርይ ከሷ ነሥቶ በልደት፥ በጥምቀት፥ በስቅለት፥ በሞት፥ በመቃብር፥ በትንሣኤ የቤዛነቱን ሥራ የፈጸመው ኀያል አምላክ ልጇ ግንቦት ፰ ቀን በምስጋና፥ በጌትነት ወደ ሰማይ ዐረገ። ግንቦት ፲፰ ቀንም መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት ሰጠ። በዚኽም፤ ነቢዩ ዳዊት፤ **"ዐረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ ወወሀብከ ጸጋከ ለዕጓለ እመሕያው።"** "ምርኮን ማርከኽ ወደ ሰማይ ዐረግኽ፤ ጸጋኽንም ለሰው ልጆች ሰጠኽ፤" ያለው ተፈጽሞበታል።

የሰው ሕሊና፥ የመላእክትም አእምሮ የማይደርስበት አምላክ በአእምሮ ፍጹማን የኾኑ መላእክት፥ ኀይሉን የሚቃወሙ አጋንንት በማያውቁት ምስጢር ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በድንግል ማሕፀን ነፍስን፥ ሥጋን ገንዘብ አድርጎ መሠረተ ድንግልናዋ ሳይናወጥ፥ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ከሷ ተወልዶ፤ ወልደ እግዚአብሔር፥ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ተብሎ ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር በትምህርት፥ በተአምራት ለሰው ዘር ራሱን ገልጾ፥ አስረድቶ፥ በመጨረሻም ተሰቅሎ፥ ሞቶ፥ ተነሥቶ በሥጋ በክብር፥ በጌትነት ወደ ሰማይ ዐረገ።

በተነሣ በ፵ ቀን ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በምሳ፥ በማእድ ከቈየ በኋላ እያነጋገራቸው ወደ ደብረ ዘይት ኼደ። እጁንም በራሳቸው ላይ እየጫነ እያንዳንዳቸውን ሾማቸው። በደብረ ዘይት ቅድስት ድንግል እናቱ የብርሃን ድንኳን ተተክሎላት ትጠብቀው ነበር። ወዳለችበት ገብቶ እሷን ካነጋገረ በኋላ ወደ ሠረገላ ኪሩቤል ወጣ ይላል የታሪክ መጽሐፍ። በዚያ ጊዜም ከቅዱሳን መላእክት የተደረገውን የክብር ሰልፍ ይዘረዝራል። እዚኽ ብዙ መዘርዘር አንችልም። ሉቃስ በወንጌሉ ስለ ጌታ በገለጠው በትንሣኤው ቀን ማታ በተገለጠላቸው ጊዜ፤ እናንተ ለዚኽ ነገር ምስክሮች ናችኹ፤ የአብን ተስፋ እልክላችኹአለኹ፤ ግን ከአርያም ኀይልን እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ቈዩ፤ ብሎ እንዳዘዛቸው ያሳይና በዕለተ ዕርገት በምሳ ላይ ሲያነጋግራቸው ከቈየ በኋላ ወደ ቢታንያ ይዟቸው እንደ ወጣ፥ እጁን በራሳቸው ላይ እየጫነ እንደ ባረካቸው፤ እየባረካቸውም ወደ ላይ እየራቃቸው እንደ ኼደ፥ እያዩት ወደ ሰማይ እንዳረገ፤ እነሱም ሰግደውለት ደስ ብሏቸው ከደብረ ዘይት ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ተመለሱ መዝግቧል። ከዚያ የቀረውን ደግሞ በግብረ ሐዋርያት በምዕራፍ ፩ ቍጥር ፫ እስከ ፲፪ ሲገልጽ፤ ከእነሱ ጋር በምሳ ላይ እያነጋገራቸው ከቈየ በኋላ ከምድር ከፍ ከፍ አለ፤ ደመና ተቀበለችው፤ እነሱም ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ሳሉ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ ከዐይናቸውም ተሰወረ፤ ብሩህ ልብስ የለበሱ ኹለት ሰዎችም ተገለጡላቸውና፦ እናንተ የገሊላ ሰዎች! ሰማይ ሰማይ እያያችኹ ለምን ከዚኽ ቆማችኋል፤ ይኽ ከእናንተ ተለይቶ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችኹት ኢየሱስ ነው፤ ዛሬ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችኹት ዳግመኛም ተመልሶ ይመጣል፤ አሏቸው። እነሱም ከደብረ ዘይት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ሲል በዐጭር ቃል ጽፎታል። ከዚኽ ሰፋ፥ ዘርዘር ያለ ትምህርት በልዩ ልዩ መጻሕፍት ይገኛል።

ይኽንንም ጌታ በመጽሐፈ ኪዳን፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ፥ በዮርዳኖስ የተጠመቀ፥ በመስቀል ላይ የተሰቀለ፥ በ፫ኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፥ በክብር በጌትነት ወደ ሰማይ ያረገ፥ በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ፥ በሙታን በሕያዋን ሊፈርድ ዳግመኛ የሚመጣ ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኀያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፤ አቤቱ ይቅር በለን፤ በሉኝ ብሎ አዝዟል። ይኽ ኹሉ የተፈጸመው እግዚአብሔር ለአዳም በሰጠው ተስፋ ከልጁ ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ሲኾን፤ ግንቦት እሷ የተወለደችበት፥ ልጇ ወደ ሰማይ ያረገበትና ቅዱስ መንፈሱን ለሐዋርያቱ የሰጠበት፥ ተስፋ ሕይወት ከፍጻሜ የደረሰበት በመኾኑ፤ የእግዚአብሔር አገር ሆይ! እግዚአብሔር ስለ አንቺ የተናገረው ነገሩ ዕፁብ ነው! ድንቅ ነው! እንድንል ያደርገናል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ሆይ! ይኽ ለቤተ ክርስቲያናችን ዐዲስ አይደለም። አንድ ነገር ልጨምርላችኹ። ጌታ ሰው ኾነ፥ ተወለደ፥ ተሰቀለ፥ ሞተ፥ ተነሣ፥ ዐረገ መባሉ ከቅድስት ድንግል እመቤታችን በነሣው አካል ባሕርይ ነው። ቀደም ሲል ስለ ዕርገት ብዙ

ነገሮች በልዩ ልዩ መጻሕፍት መጻፋቸውን፥ ከዚኽ ያላጠቃለልናቸው መኾኑን ገልጬአለኹ። ግን አንድ ላስታውሳችኹ። ይኸም የግላችን ነው። ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ስለ ዕርገት በተናገረው ድጓው፤ **“ጸርኀ ገብርኤል እምሰማይ ዘይብል ፃኡ ተቀበሉ መጽአ ወልደ አምላክ ለቢሶ ሥጋ ማርያም ወፄዊዎ ነፍሳተ ዓለም።”** “መልአክ ገብርኤል ከሰማይ ኾኖ፦ መላእክት! የአምላክ ልጅ የማርያምን ሥጋ ለብሶ የዓለምን ነፍሳት ማርኮ መጥቷልና ውጡ ተቀበሉ ብሎ ዐወጀ፤” ይላል። ይኼ ነው እንግዲኽ የቅድስት ድንግል ዝርዝር ታሪክ። የልጇ የቤዛነት ሥራ። በሚገለጥበት ኹሉ የሷን ሕይወት የማይዳስስ ነገር የለም። እንግዲያውስ አኹንም ዕፁብ ዕፁብ ከማለት በቀር ወደ ስሕተት መግባት የለብንም።

ወንድሞቼ! እመቤታችንን ቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክን ከሰው የሕይወት መሥመር ልዩ የሚያደርጋት ይኸ ምርጫ ነው። ስለዚኽም ስለሷ የተጻፈው ኹሉ ምሳሌውም ንግግሩም ለሷ ብቻ ነው። ሌላ አይጨምርም። ስለ ሌላው የተጻፈው ደግሞ እሷን አይጨምርም። እነ ቄስ አስተርአየና እነ አባ የጠቀሱት ጥቅስ ራሳቸውንና መሰሎቻቸውን የሚመለከት እንጂ ቅድስተ ቅዱሳንን የሚመለከት አይደለም። የሚገርመው ደግሞ ቀሳውስት ነን፥ ጳጳሳት ነን እያሉ መበሥሩ መልአክ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፤ **“ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት፤”** “ደስ ያለሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው፤ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤” ያለውን ቃል ችላ ብለው፥ ንቀው፥ ጠቅጥቀው፤ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ስለ በደለኞች የጻፈውን ስለ ቅድስተ ቅዱሳን፥ ስለ ንጽሕተ ንጹሐን አድርገው መጥቀሳቸውና መጻፋቸው ነው። ከዚኽም ጋራ፤ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የጻፈውን፥ በሃይማኖተ አበው የተገለጠውን ስለ እመቤታችን፤ **“ተፈሥሒ ኦ ማርያም እንተ ብኪ ተበትከ ማዕሠረ ሔዋን ማሕመሚ እንደ ገደፉ እግዚአብሔር ውስተ ደይን።”** “እግዚአብሔር በደይን የጣላት ጽኑ የሚጐዳ የሔዋን ማሰሪያ ባንቺ የተቈረጠላት ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ፤” ሲል የተናገረውን አበው ኹሉም እንዲለምደው በተአምረ ማርያም መቅድም ጽፈው ለቤተ ክርስቲያን ያስተላለፉት በመኾኑ እስከ ዛሬ ተአምር በሚነበብበት ጊዜ ኹሉ ይኸ ቃል በመነበብ ላይ እያለ ቄሱና ጳጳሱ ግን ይኸን ዐልፈው፤ **“ወሶበ ዐለውነ ትእዛዞ በምክረ ከይሲ ርጉም ወፃእነ እምገነት ተድላ ውስተ ሙስና።”** “በርጉም ከይሲ ምክር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባፈረስን ጊዜ ከገነት ወጣን፤ ወደ ጥፋት ደረስን፤” ሲል ስለ በደለኞች የተናገረውን ለእመቤታችን ሰጥተው መጻፋቸው እጅግ በጣም አሳፋሪ ነው።

እኔ እግዚአብሔር በፈቀደልኝ ጥሪ በዚኽ ሥራ ከቆምኩበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እናታቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያመነችበትን፥ የምታምንበትን፥ የተማረችውን፥ የምታስተምረውን እስከ ዓለም ፍጻሜም የማይለወጠውን እውነተኛ ትምህርቷን ለትውልዱ ለማስተላለፍ ከዚኽ በፊት የጻፍኳቸው መጻሕፍት አንዳሉ ታውቃላችኹ። አኹን ደግሞ ይኸን መጽሐፍ የጻፍኩላችኹ ልባቸው ከትዕቢት ያለፈ፥ አፋቸውን በሰማይ ያኖሩ፥ ምላሳቸውን በምድር ላይ የሚያውለበልቡ ክፉዎች እየጨመሩ ስለ ኼዱ ራሳችኹ እንድትጠበቁ፥ አገራችኹንም ከጥፋት እንድታድኑ ነው።

ምእመናን! ዓለም ወደ ጥፋት እየኼደ ነው። ጌታ በወንጌል፥ ሐዋርያት በመልእክቶቻቸው የተናገሩት ኹሉ በዓለም ከሥራ ላይ እየዋለ ነው። ይልቁንም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በኹለተኛ መልእክቱ ምዕራፍ ፪ እና ፫ የገለጠው፥ ሐዋርያው ዮሐንስም በራእዩ ምዕራፍ ፲፮ የመዘገበው፤ በይበልጥም ከቍጥር ፲፪ እስከ መጨረሻው የገለጠው በሥራ ላይ፥ በኺደት ላይ ነው። ይኹን እንጂ ያም ኾኖ ሃይማኖት ካለው የሚድን እንዳለ፤ “እነሆ እኔ እንደ ሌባ ድንገት እመጣለኹ፤ ራቁቱን ኾኖ ዕርቃኑ ተገልጦበት እንዳያፍር ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው፤” የሚል ቃል ተስፋ በቍጥር ፲፭ ላይ ተመዝግቧልና ኢትዮጵያውያን ኹሉ የማይጠቅማችኹን የሃይማኖት ትምህርት መቀላወጥና ማግበስበስ ትታችኹ በእናት ቤተ ክርስቲያናችኹ እምነትና

ትምህርት ጸንታችኹ አገራችኹንም ራሳችኹንም ትውልዳችኹንም እንድታድኑ ዐደራ እላለኹ።

የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የዐድዋን ጦርነት ተከትሎ፥ የኹለተኛው የዓለም ጦርነት በፋሺስት በማይጨው የተነሣውን ጦርነት ተከትሎ መምጣቱን ልብ የሚያደርግ ሰው ይኽን የኢትዮጵያን ውድቀት ተከትሎ ሦስተኛው የዓለም ጦርነት መቅረቡን፥ ያም ሃይማኖት የሌለው ኹሉ የማይድንበት መኾኑን፥ በውስጡ ሦስት መልክ ይዞ የተዘረጋው የቅጣት የሰልፍ መሥመር ማንም ሊከላከለው የማይችል ነውና ከመድረሱ በፊት ብንጠነቀቅ መልካም ነው። ኢትዮጵያውያን ካህናትም ምእመናንም ስሙኝ! ስሙኝ! ስሙኝ! የእግዚአብሔር ያለኽ! ራሳችኹንም አገራችኹንም አድኑ።

እኛ ስለ ሰደብናት እኛ እንጠፋለን እንጂ የቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ ማርያም ክብሯ፥ ልዕልናዋ አይቀነስም፤ አይገሰስም። ቅዱስ እግዚአብሔር ልጇ ቅድስት ድንግል፥ ቅድስተ ቅዱሳን፥ ንጽሕተ ንጹሐን፥ ልዕልት እምኵሉ ፍጥረት አድርጎ ፈጥሯታል። ማንም ሊወስድባት የሚችል የለም። በዚኽም ዓለም፥ በመንግሥተ ሰማይም የሷ ብቻ ነው። ከዚኽ ጋራ ኢትዮጵያውያን ኹሉ እመቤታችን ኢትዮጵያን በስደት በጐበኘችበት፥ በጣና ደሴቶች በቈየችበት ጊዜ አገሪቱን ርስት፥ ሕዝቧን ዐሥራት አድርጎ ኀያል ልጇ በቃል ኪዳን የሰጣት ስለ ኾነ ይኽን ክብር በገዛ እጃችን እንዳናጣ እንጠንቀቅ የሚለውን ድምፄን አሰማለኹ።

ይኽን መጽሐፍ በቸርነቱ አስጀምሮ፥ በቸርነቱ ላስፈጸመኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው። በጉልበትም፥ በሀብትም የረዱኝን ኹሉ እግዚአብሔር ይርዳቸው። **ስብሐት ለኪ ኦ ወላዲተ እግዚአ ኵሉ፤ አኰቴት ወክብር ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን። ወልድኪ ሣህሎ ይክፍለነ አሜን።**

አለቃ አያሌው ታምሩ።

ይህ ጽሑፍ የተገኘው «ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ፤ ግንቦት፥ ልደታና ዕርገት» ከተባለው የአለቃ አያሌው ታምሩ መጽሐፍ ገጽ ፷፬ — ፹፪ ነው።